የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አ፲፯ኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 34
ADDIS ABABA 11th May 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫

የፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ................................ ገጽ ፭ሺ፰፻፭

## CONTENTS

Regulation No 210/2011

Federal Universities Council of Ministers Regulation ..................................... Page 5805

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫

## ስለፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፺፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ::

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ::

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩) "አዋጅ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ ነው፤

፪) በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ፤

፫) " ፌዴራል ዩኒቨርሲቲ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፭(፩) እና አንቀፅ ፱(፩) መሠረት የተቋቋመ ዩኒቨርሲቲ ነው ፤

፬) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል ::

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 210/2011

## FEDERAL UNIVERSITIES COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 97 (1) of the Higher Education Proclamation No 650/2009.

1. **<u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210./2011".

2. ***<u>Definitions</u>***

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1) "Proclamation" means the Higher Education Proclamation No. 650/2009;
2) the definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;
3) "federal university" means a university established in accordance with Article 5(1) and Article 9(1) of the Proclamation;
4) any expression in the masculine gender includes the feminine.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 6.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫. <u>የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ዓላማ</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፬ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩) ዕውቀትን የማፈላለግ ፣ የማበልጸግ ፣ የማቀብና የማስተላለፍ ፤

፪) በተለያዩ መስኮች የቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞችን የመስጠት ፤

፫) ለቴክኖሎጂ ሽግግር ቅድሚያ በመስጠት ምርምርና ጥናቶችን ማከናወንና ውጤቱን የማስረጽ ፤

፬) የሕብረተሰብና ሌሎች የማማከር አገልግሎቶችን እንደሁኔታው በነፃ ወይም በክፍያ የመስጠት ።

፬. <u>የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ኃላፊነት</u>

የአዋጁ አንቀጽ ፰ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩) የትምህርት ክፍሎችን የማቋቋም፣ የማደራጀትና ደረጃቸውን ፣ ተግባራቸውንና ኃላፊነታቸውን የመወሰን እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመዝጋት ፤

፪) በአገሪቱ ፍላጎት መሠረት የቅድመ ምረቃና ድሕረ ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና አጫጭር ስልጠናዎችን የመቅረጽና የመስጠት ፤

፫) የምርምር ውጤቶችን የማሳተምና የማስረጽ ፤ በምርምር ውጤቶች ላይ ለመምከር የውይይት መድረኮችን የማዘጋጀትና የማካሄድ ፤

፬) የአካዳሚክ መጽሔቶችንና የአካዳሚክ ዜና ማሳወቂያን የማቋቋምና የማስተዳደር ፤

፭) የዩኒቨርሲቲውን መምህራን የትምህርት ደረጃ የማሳደግ እና የመምህርነት ሙያዊ ብቃታቸውን በቀጣይነት የመገንባት ፤

፮) የሌሎች መንግሥታዊና ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ተቋማት የማስፈጸም አቅምን መገንባት ላይ አስተዋፆ የማድረግ ፤

፯) የምክር አገልግሎቶች ለመንግሥት ፣ ለኢንዱስትሪዎችና ለህብረተሰቡ የመስጠት ፤

፰) ዘመናዊ የቤተመጻህፍት አገልግሎትን በማደራጀት ለተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ፤

፱) በትምህርት አግባብነትና ጥራት ጉዳዮች ላይ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር ፤

፲) አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢ ክፍያን የማስከፈል ፤

፲፩) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን ።

3. ***Objectives of Federal University***

Without prejudice to the provisions of Article 4 of the Proclamation, a federal university shall have the following objectives:

1/ to search for, cultivate, preserve and transmit knowledge;

2/ to offer undergraduate and graduate programs in various fields;

3/ to conduct research and studies primarily focusing on technology transfer and disseminate the results thereof;

4/ to provide services to the wider community through professional and consultancy works, free of charge or with remunerations as the case may be.

4. ***Responsibilities of Federal University***

Without prejudice to the provisions of Article 8 and other applicable provisions of the Proclamation, a federal university shall have the following additional responsibilities:

1) to establish, organize and determine the status, functions and responsibilities of academic units, and to close down any of them when appropriate;

2) to design and implement undergraduate and graduate programmes and short-term trainings in accordance with the needs of the country;

3) to publish and disseminate research works as well as hold discussion forums to deliberate upon the results;

4) to establish and run academic journals and newsletters;

5) to upgrade the qualifications of its academic staff and enhance continuously their professional competency;

6) to contribute specially to the institutional capacity building of other public and non-profit-making private institutions, including the upgrading of the qualifications of their academic staffs;

7) to provide consultancy services to government, industries and communities;

8) to organize modern library services and provide access to entitled users;

9) to cooperate with the Agency on education relevance and quality matters;

10) to charge appropriate fees for its services when warranted;

11) to carry out such other activities that accord with its objectives.

፭. የተቋም ነፃነትና ተጠያቂነት

፩) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ የተሰ ጠው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ተጠያቂነት ይኖረዋል ፡፡

፪) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮውን በሚገባ ስለማ ሳካቱ በተለይም የሚከተሉትን ስለማረጋገጡ ተጠያ ቂነት ይኖርበታል፡-

ሀ) የሚያካሄዳቸው የትምህርትና የምርምር ፕሮግ ራሞች አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሚመሩ መሆናቸውን እና ተገቢውን የጥራት ድረጃዎች የጠበቁ መሆናቸውን ፤

ለ) የትምህርት፣ የስልጠናና የምርምር ፕሮግራሞቹ ትኩረት ለመንግሥት ፕሮግራሞች ቅድሚያ የሚሰጡ ከሀገራዊ ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ መሆናቸውን ፤

ሐ) የመማር ማስተማርና የምርምር ሥራዎቹ እና አጠቃላይ አሠራሩ ተቋማዊ ሥርዓት ያላቸውና በመልካም አስተዳደር መርሆዎች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ፤

መ) አስተማማኝ የገቢ ማመንጫት አቅም መገን ባቱንና የበጀትና ሃብት አደላደሉና አጠቃቀሙ ወጪ ቆጣቢና ዓላማውንና ኃላፊነቱን በማሳካት ውጤታማ መሆኑን ፤

ሠ) የራሱን አፈጻጸም ባጠቃላይ እና የትምህርት ክፍሎቹንና የአካዳሚክ ሠራተኞቹን አፈጻጸም በተለይ አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ መልካም ልምዶች ላይ በተመሠረቱ መመዘኛዎች ወቅቱን ጠብቆ የሚለካና አፈጻጸ ሙን በቀጣይነት የሚያሻሽል መሆኑን ፤

ረ) የትምህርት ክፍሎችን አስተዳደራዊ ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ተቋማዊ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን፤ እንዲሁም የመላ ዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት የአስተዳደር ነፃነት የተሰጣቸው የአካዳሚክ ክፍሎችን አፈፃፀም ከዩኒቨርሲቲው ዓላማና ሃላፊነት ጋር ስለመጣጣማቸው በሚገባ የሚቆጣጠሩ መሆናቸውን፤

ሰ) ተቋማዊ ነጻነቱንና የአካዳሚክ ነፃነቱን አግባብ ካልሆነ አጠቃቀም የሚከላከል መሆኑን ፤

ሸ) የጥራት ደረጃውንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ የአፈ ጻጸም ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት የሚያ ቀርብ መሆኑን ፡፡

፮. ስለዩኒቨርሲቲ ሴኔት

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፵፱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ሴኔት የሚከተሉት ተጨማሪ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚያወጣቸውን የአካዳሚክ አጠቃላይ መመሪያዎችን ተግባራዊ የማድረግ ፤

ለ) የተማሪዎች የአካዳሚክና የዲስፕሊን ጉዳዮችን የሚመለከቱ መመሪያዎችን አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የማውጣት ፤

ሐ) የአካዳሚክ ሠራተኞች ጉዳዮች የሚመሩበት መመሪያዎችን አግባብነት ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የማውጣት፤ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን የመገምገም ፡፡

5. *Autonomy and Accountability*

1) A federal university shall enjoy the autonomy provided for by Article 17 of the Proclamation with the accountability as provided for under sub-article (2) of this Article.

2) A federal university shall have accountability for fulfillment of its objectives and responsibilities, and more specifically whether:

a) it conducts its education and research programmes consistent with the applicable provisions of the Proclamation and maintains appropriate quality standards;

b) its education and research academic programmes accord priority to government programmes and to the country's needs and objective conditions;

c) its teaching-learning and research activities, and its operations in general, have been institutionalized and are conducted in accordance with principles of good governance;

d) it has built reliable sources of income generation and the allocation and utilization of its budget and assets ensure efficiency and effectiveness in achieving its objectives and responsibilities;

e) it measures with periodic regularity its own performance in general and the performance of its academic units and academic staffs in particular against standards based on appropriate international benchmarks and improve its performance continuously;

f) it has established reliable institutional systems that ensure the autonomy of its academic units with due accountability; and the university-wide structures supervise effectively that the performance of autonomous academic units is consistent with the university's objectives and responsibilities;

g) it is able to prevent abuse of its autonomy and academic freedom;

h) it submits, regularly performance reports of good quality to appropriate bodies.

6. *University Senate*

1) Without prejudice to the provisions of Article 49 of the Proclamation, the senate of a federal university shall have the following additional responsibilities:

a) to implement academic general guidelines issued by the university's board;

b) to issue rules on student academic and disciplinary matters in accordance with the applicable provisions of the Proclamation;

c) to issue rules governing academic staff affairs in accordance with the applicable provisions of the Proclamation and evaluate the implementation of same.

፪) ሴኔቱ ኃላፊነቱን አግባብነት ላላቸው የዩኒቨርሲቲው አካላትና ለሚያቋቁማቸው ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴዎች በውክልና ማስተላለፍ ይችላል ፡፡

፫) በአዋጁ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌዎች መሠረት ለዩኒቨርሲቲ ቦርድ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ሴኔት በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት፤
ለ) የዩኒቨርሲቲው የምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት፤
ሐ) የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ፤
መ) የዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ወይም የኢንጂነሪንግ ፋኩልቲ (ትምህርት ቤት) ዲን ፤
ሠ) የዩኒቨርሲቲው ዋና ሬጂስትራር፤
ረ) የዩኒቨርሲቲው የቤተመጻህፍት ኃላፊ፤
ሰ) በግል ብቃታቸውና በአካዳሚክ ማዕረጋቸው ቀዳሚነት ላይ ተመሥርቶ የሚመረጡ ከአስራ ሁለት እስከ ሃያ አምስት የሚደርሱ የአካዳሚክ ክፍሎች ኃላፊዎች እና/ ወይም መምህራን፤
ሸ) የዩኒቨርሲቲው መምህራን ማኅበር ሁለት ተወካዮች ፤
ቀ) የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ማኅበር ሁለት ተወካዮች ፡፡

፬) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተራ ፊደል (ሰ) የተመለከቱት የሴኔቱ አባላት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚወስነው አሠራር መሠረት በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ተመርጠው የሚመደቡ ይሆናሉ ፡፡

፭) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተራ ፊደል (ሰ) እስከ (ቀ) የተመለከቱት የሴኔት አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ እንደአግባብነቱ በድጋሚ አባል ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

፮) የሴኔት አባልነት በተቻለ መጠን ጾታዊ ስብጥርና መመጣጠን እንዲኖረው የሚደረግ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተራ ፊደል (ሸ) እና (ቀ) የተመለከቱት አባላት እኩል የፆታን ተዋጽኦ መሠረት ያደረገ ይሆናል ፡፡

፯) ያለ ድምጽ በቋሚነት የሚሳተፉ የሴኔት አባላት ጉዳይ በሴኔቱ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

፯. ስለዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትነት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንትነት በዕጩነት የሚቀርብ ተወዳዳሪ፡-

ሀ) ኃላፊነቱን ለመቀበል ፈቃደኝነት ያለው ፣ እና
ለ) በመልካም ሥነምግባሩ የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ እምነት የሚጥልበት፤

መሆን አለበት፡፡



2) The senate may delegate its responsibilities to the appropriate organs of the university and to ad hoc or standing committees it may establish.

3) Without prejudice to the provisions of Article 50 sub-article (4) of the Proclamation on the powers of a university board, the senate, which shall be chaired by the president of the university, shall have the following members:

a) the academic vice president of the university;
b) the vice president of the university for research;
c) the vice president of the university for administration and development;
d) the scientific director of technology institute or engineering faculty (school) head of the university;
e) the university registrar;
f) the university librarian;
g) twelve to twenty-five leaders of academic units and/or academic staffs selected on the basis of their individual merit and academic seniority;
h) two representatives of the university teachers' union;
i) two representatives of the university students' union.

4) The senate members mentioned under paragraph (g) of sub-article (3) of this Article shall be appointed by the president of the university through procedures established by the university's board.

5) Without prejudice to the generalities of sub-article (3) of this Article the tenure of membership of the senate members listed under paragraphs (g) to (i) of sub-article (3) of this Article shall be three years; provided, however, that they may be re-appointed as may be appropriate.

6) The senate members listed under paragraphs (h) and (i) of sub-article (3) of this Article shall be based on gender parity, while senate membership generally shall ensure gender mix and balance to the extent possible.

7) The senate shall decide on issues of non-voting senate members.

7. ***President and Vice Presidents***

1) Without prejudice to Article 52 of the Proclamation, a person to be nominated to the post of president or vice president of a federal university shall meet the following additional requirements:

a) has the willingness to shoulder the responsibility; and
b) has good moral and ethical standards to command respect and confidence in the university community.

፪) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የውድድርና ምርጫ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) ተገቢው ሽፋን ያለውና በቂ ጊዜ የሚሰጥ የውድድር ማስታወቂያ ይወጣል ፤

ለ) የመመዘኛ መሥፈርቱን የሚያሟሉ ቢያንስ ሦስት ዕጩዎችንና የተወዳዳሪዎችን ሙሉ ዝርዝር ያካተተ የውሳኔ ሃሳብ ለፕሬዚዳንትነት ሲሆን ለዚሁ ተግባር በዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተሰየመ ኮሚቴ ወይም ለምክትል ፕሬዚዳንትነት ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በተሰየመ ኮሚቴ ለቦርዱ ይቀርባል ፤

ሐ) ቦርዱ የሌሎች ሁለት ተፎካካሪ ዕጩዎች መረጃንም ጨምሮ ለፕሬዚዳንትነት ይበልጥ እንደሚመጥን ያመነበትን ዕጩ እንዲሾም ለሚኒስትሩ ያቀርባል ።

፫) ቦርዱ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች አፈጻጸም ዝርዝር መመሪያ ያወጣል ።

፬) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ዐ) መሠረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተለይቶ ውክልና ሲሰጠው በዩኒቨርሲቲው ቦርድ የሚወሰን ይሆናል ።

፰. <u>የፕሬዚዳንት ኃላፊነት</u>

የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በአዋጁ አንቀጽ ፶፫ ከተደነገጉት በተጨማሪ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩) የዩኒቨርሲቲውን የአፈጻጸም ሪፖርቶች በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ጸድቀው ወይም ቦርዱ በሚሰጠው አመራር መሠረት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል ፤

፪) የዩኒቨርሲቲውን ቦርድ አጀንዳዎች የቦርዱን ሰብሳቢ በማማከር ያዘጋጃል፣ የቦርዱን ስብሰባዎች የሚያሳልጡ ቅድመ ዝግጅቶችን ያከናውናል፣ የቦርዱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል ፤

፫) በአዋጁ አንቀጽ ፶፰ መሠረት የመንግሥት ተቋማት የምክክር መድረክ እንዲቋቋምና ተልዕኮውን እንዲወጣ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል።

፱. <u>የምክትል ፕሬዚዳንት ኃላፊነት</u>

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፣ ማንኛውም የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት የተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በሥራ ላይ ለማዋል በሥሩ ያሉ ክፍሎችን ይመራል፣ ይቆጣጠራል ፤

2) The system of nomination and appointments of the president and vice presidents of a federal university shall be as follows:

a) vacancy announcement shall be made with due regard to its accessibility and appropriateness of its duration;

b) nominations of qualified candidates shall be submitted to the university's board by a committee established by the board for the post of the president or by a committee established by the president for the post of a vice president, in either case with a short-list of at least three suitable candidates accompanied by the long list of candidates;

c) the board shall nominate the most meritorious candidate and submit its nominations to the Minister for the post of the president; and such submission shall include documented information on two other competitive candidates.

3) The board shall determine by directive the particulars of the system of nomination and selection of candidates provided for under sub-article (1) and (2) of this Article.

4) The remunerations and other benefits of the president and vice presidents of a federal university shall be determined by the Council of Ministers or by the university's board as may be specifically delegated by the Council of Ministers in accordance with the provisions of paragraph (t) of sub-article (1) of Article 44 of the Proclamation.

8. ***<u>Responsibilities of the President</u>***

Without prejudice to Article 53 of the Proclamation, the president of a federal university shall have the following additional responsibilities:

1) to submit timely to appropriate bodies the university's performance reports as approved or may be directed by the university's board;

2) to prepare the agenda for the university's board sessions in consultation with the chairperson; to make advance preparations to facilitate the board's sessions; and to execute the board's decisions;

3) to play his due role in the establishment and running of the Forum for Public Institutions, which shall be established and function in accordance with the provisions of Article 58 of the Proclamation.

9. ***<u>Responsibilities of the Vice President</u>***

1) Without prejudice to sub-article (1) of Article 54 of the Proclamation, a vice president of a federal university shall have the following responsibilities:

a) to direct and supervise units accountable to him in the execution of decisions and directives of the governing bodies of the university;

ለ) በሥሩ ያሉ ክፍሎች ዕቅዶች ዝግጅትን ይመራል ፤ የዕቅዱን አፈጻጸም በበላይነት ይቆጣጠራል ፤

ሐ) በኃላፊነቱና ተግባሩ መሠረት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችን ይመሰርታል ፣ አፈጻጸ ማቸውን ይከታተላል ፤

መ) በሥሩ ያሉ ክፍሎችን የሥራ አፈጻጸምና በጀት አጠቃቀም በተመለከተ ለፕሬዚዳንቱ ሪፖርት ያቀርባል ።

፪) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንቶች የውጭ ጉዞ አስቀድሞ በዕቅድ የተያዘ ወይም በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በተለየ ሁኔታ የተፈቀደ ሆኖ የክንውን ሪፖርት የሚቀርብበት ይሆናል ።

፲. ልዩ የተማሪ ቅበላ

፩) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በአዋጁ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌዎች መሠረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ዝግጅታቸው፣ በአጠቃላይ ዕውቀታቸውና በሥራው ዓለም ተሞክሮአቸው ለቅድመ ምረቃ ትምህርት ብቁ የሆኑ ጎልማሶችን በልዩ የቅበላ ሥርዓት በተፈቀዱ መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞቹ ሊቀበል ይችላል ።

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጎልማሶች ልዩ የቅበላ ሥርዓትን መዘርጋት የሚቻለው የፍላጎት ጥናት በማድረግና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመፈተሽ አስፈላጊነቱንና ሊፈጸም የሚችል መሆኑን ዩኒቨርሲቲው ሲያረጋግጥ ይሆናል ።

፫) የጎልማሶች ልዩ የቅበላ ሥርዓቱ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ውሳኔና የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይሆናል ።

፬) ለቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ጎልማሶች የሚመለመሉት የትምህርት መስኩ የሚጠይቀውን ብቃት የሚለካ የመግቢያ ፈተና በመስጠት ይሆናል ።

፭) በዩኒቨርሲቲው ቦርድ በተወሰነ አሠራር መሠረት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ግለሰቦችን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከክፍያ ነፃ ለማድረግ ካልወሰነ በስተቀር በልዩ የቅበላ ሥርዓት የሚስተናገዱ ጎልማሶች የመግቢያ ፈተናን እና የትምህርትን ወጪዎችና ሌሎች ክፍያዎችን በራሳቸው እንዲሸፍኑ ይደረጋል ።

፮) በአዋጁ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ የተወሰነላቸውን ተማሪዎች የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በዓቅሙ ልክ የመቀበልና ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርበታል።

b) to lead preparations of plans of activities of units accountable to him and supervise the implementation of the plans;

c) to establish national and international linkages in accordance with his responsibility and monitor their implementation;

d) to submit reports to the university's president on performance and budget utilization of the units accountable to him.

2) Foreign travels by any vice president of a federal university shall be preplanned or as may be specifically approved by the university's president; and submission of reports on foreign travels shall be mandatory.

10. ***Special Student Admission***

1) Consistent with the provisions of Article 39 sub-article (5) of the Proclamation, a federal university may admit through a special admissions system to its non-formal programmes experienced students who are fit for undergraduate studies in their English language proficiency, general knowledge and work experience.

2) A system of special admissions for experienced students in accordance with the provisions of sub-article (1) of this Article may only be instituted upon establishing, by the university, its necessity and feasibility through a proper study of needs and assessment of international good practice.

3) The special admissions system shall be implemented in accordance with the decision and directives of the university's senate.

4) The fitness for undergraduate studies of experienced students shall be assessed through an appropriate entrance examination specific to the field of study.

5) Unless the university's president decides, in accordance with rules and procedures approved by the university's board, to waive payments partially or fully, the beneficiaries of the special admissions procedure for experienced students shall cover the expenses for the administration of the entrance examination as well as tuition and other fees.

6) A federal university shall have the responsibility to admit, within the limit of its intake capacity, students entitled to affirmative action in accordance with the provisions of Article 39 sub-article (4) of the Proclamation, and provide the necessary assistance to them.

፲፩. **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

፩) ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፪) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ በቦርዱ የጸደቀ የራሱ አርማና ማህተም ይኖረዋል ፡፡

፫) የፌዴራል ዩኒቨርሲቲ ቦርድ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ረ) የተሰጠውን ሥልጣን የፌዴራል ዋናው ኦዲተርን ምክር መሠረት አድርጎ ይፈጽማል ፡፡

፲፪. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

**11. *Miscellaneous Provisions***

1) The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

2) A federal university shall have its own logo and seal approved by its board.

3) The board of a federal university shall exercise its powers provided for by paragraph (f) of sub-article (1) of Article 44 of the Proclamation in accordance with advice by the Federal Auditor General.

**12. *Effective Date***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 11th day of May, 2011.

*MELES ZENAWI*
*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*